Gaafa: 21/01/2017
Date: تاريخ

Lakk.:02/stm/abo/2017
No.: رقم

## ህዝቦችን ማናቆር የወያኔ መንግስትን እድሜ ይበልጥ ያሳጥራል

(*ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር የተሰጠ መግለጫ*)

ኢትዮጵያ ከህዝቦች ፍላጎት ውጪ በሃይል የተመሰረተች ኢምፓዬር ናት። በሃይል ከመመስረቷ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የፖለቲካ ችግርም ለቅኝ ኣገዛዝ የተዳረጉትን ህዝቦች መብት ነፍጎ በራሳቸው እድል ላይ ወሳኝ እንዳይሆኑ ኣደረጋቸው። የገዢዎችን ፍላጎት ብቻ ለማሟላት የተዘረጉት ስርዓቶችም ጸረ-ዲሞክራሲ በመሆን ጭቆናና ዝርፊያን ኣስፋፍተዋል። ህዝቦችን ለድህነት፥ ኋላቀርነትና ረሃብ ዳርጓቸዋል። ለረዥም ዓመታት የቆየው የፖለቲካ ችግር ለእድገትና ብልጽግና እንቅፋት ሆኖ የህዝቦችን ህይወት መራር ኣደርጎታል። ይህችን ኢምፓዬር ኣንቆ ለያዛት ችግር መፍትሄ ማፈላለግ በሃይል ወደ ስልጣን የመጡ መንግስታት ፍላጎት ባለመሆኑ ይህ መፍትሄ የተነፈገው ችግር ኢምፓዬሪቷን ጠፍሮ በመያዙ ዜጎቿ የሚያፍሩባት ሃገር ሆናለች።

በሃይለስላሴ ዘመን በረሃብ የምትታወቀዋ ኢትዮጵያ በደርግ ዘመንም የረሃብ ሃገር በመሆን ትታወቃለች። በፋሽስቱ የወያኔ/ሕወሃት መንግስት ስርም በኣለም ዘንድ የምትታወቅበት ስሟ እንደቀጠለ ይገኛል። ሚሊዮኖች በረሃብ የሚሰቃዩባትና በእርጥባን ህይወታቸውን የሚያቆዩባት ኢምፓዬር ሆና ቀጥላለች። የወያኔ መንግስት ልመናን እንደመብትና እንደብልህነት እንጂ እንደኣስነዋሪ ተግባር ኣይቆጥረውም። በረሃብ ተጠቂዎች ስም የሚገኘውን ሃብት የኣገዛዝ እድሜውን ለማራዘም እንደሚያውለው ሁሉ ረሃብን ህዝቦችን ለማንበርከክ እንደስልጣን ዘመን ማራዘሚያ ስልት ስለሚጠቀምበት መቸውም ቢሆን ረሃብ ከዚህች ኢምፓዬር ይጠፋል ተብሎ ኣይታሰብም።

ከረሃብና ድህነት በተጨማሪ ሁሉም የኢትዮጵያ ኢምፓዬር ሃብት በወያኔ/ሕወሃት ቁጥጥር ስር መግባቱ ህዝቦችን ለኣመጽ እያነሳሳ ነው። የኣናሳ ቡድን የበላይነትን ለማስጠበቅ ሲባል የሚካሄደው የዘር ኣድልዎ ሁሉንም ተጨቋኝ ህዝቦች **ይብቃ!** ብለው ለመብታቸው እንዲፋለሙ በማድረግ ላይ ይገኛል። በተለይ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ የሃገር ባለቤትነትና የዲሞክራሲ መብት ጥያቄ በማንሳት እያካሄደ ያለው ፍልሚያ ይህንን ኣምባገነን መንግስት ከማጋለጥ በተጨማሪ መሰረት የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ውድቀቱን በማፋጠን ላይ ይገኛል።

ማንኛውም ኣምባገን መንግስት በተጨቋኞች ክንድ ከስልጣን እስካልተወገደ ድረስ የኣገዛዝ ስርዓቱን ለማስቀጠል ይፈይደኛል ባላቸው ስልቶች ሁሉ ይጠቀማል። ህዝቦችን በማናቆር ስልጣኑን ለማቆየት ይሻል። በሚፈጽመው የግድያ፥ የእስራትና የማስፈራሪያ እርምጃ እስትንፋሱን ለማቆየት ይፍጨረጨራል። **“እኔ ከሌለሁ ሃገር ተበታተናለች፥ ህዝቦች ይጨራረሳሉ”** በሚል የሃሰት ዲስኩር ውዥንበር ማንገስና ማባበልም ገዢዎች የሚጠቀሙበት ስልት ነው።

ፋሽስቱ የወያኔ/ሕወሃት መንግስት በህዝቦች እርምጃ በተለይ የኦሮሞ ህዝብ በቀጣይነት እያካሄደ ባለው የኣልገዛም-ባይነት ኣመጽ መሽመድመዱ ከማንም የተሰወረ ኣይደለም። ወያኔ በኣብላጫው ከኣንድ ኣካባቢ በተሰባሰቡ ተማኝ የጦርና የደህንነት ሃይል ላይ በመመርኮዝ ከሌሎች ብሄሮች የተወለዱትን ደግሞ በጊዜያዊ ጥቅም ከጎኑ ኣሰልፎ በተላላኪት እየተጠቀመባቸው ያለ መንግስት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ውስጡ በስብሶ ውድቀቱ ኣይቀሬ መሆኑ የተረጋገጠው መንግስት ከሃይል በተጨማሪ በምዕራባውያን መንግስታት ልገሳና ምርቃት የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም እየጣረ ነው። እስትንፋሱን ለማቆየት እያደረገ ባለው በዚህ ከንቱ ጥረት የኦሮሞን ህዝብ ዋነኛ ጠላቱ ኣድርጎ በመፈረጅ በጭካኔ የተሞላ ሁሉን ኣቀፍ ዘመቻ በሁሉም ኣቅጣጫ ከፍቶበታል። በኦሮሞ ህዝብ ላይ ከተከፈተው ሰፊ ዘመቻ ውስጥ ኣንዱ የኦሮሞ ህዝብ ጸር የሆነውን ሃይል **"ልዩ ፖሊስ"** በሚል ከሶማሌ ብሄረሰብ የተውጣጡና ድብቅ ዓላማ ያነገቡ ታጣቂዎችን በማደራጀት በጄኔራል ኣብረሃ ቁራቴሪ ኣዛዥነት የኦሮሞ ህዝብ ላይ እንዲዘመቱ ማድረግ ነው።

በኣሁኑ ወቅት በምስራቅ ኦሮሚያ በሶማሌ ድንበር ኣካባቢ፣ በደቡብ-ምስራቅና በደቡብ ኦሮሚያ የሚገኝ የኦሮሞ ህዝብ በ**ልዩ ፖሊስ**ና በስርዓቱ ሃይሎች የከፈተበትን ጦርነት በመመከት ላይ ይገኛል። የወያኔ መንግስት ይህን ለስርዓቱ እንዲዋጉ ያሰለፈውን ሃይል የኦሮሞን መሬት እንድይዙ በማድረግ በኦሮሞ ህዝብ መሬት ላይ የሶማሌ ክልል ባንዲራን በማስተከል ላይ ይገኛል። የሶማሌ ዜጎች ወያኔ ህዝቦችን በማጋጨት የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየሸረበ ያለውን ሴራ ባለማወቅም ይሁን በማወቅ የህዝቦች ጠላት ለሆነው መንግስት መሳሪያ በመሆን በኦሮሞ ህዝብ ማንነትና መሬት ላይ መዝመት ኣሳፋሪና በታሪክና በህግ ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

በምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በባሌ ቆላማ ኣካባቢዎች፣ በቦረናና በጉጂ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ጦርነት የኦሮሞን መሬት ብቻ ሳይሆን በኦሮሞ ህዝብ ማንነት ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ በኦሮሞ ማንነት ላይ የተከፈተው ዘመቻም ጦርነቱ እየተካሄደበት ባሉ ኣካባቢዎች የሚገኙ ኦሮሞዎች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የኦሮሞ ዜጎች የሚመለከት ነው። በመሆኑም ሁሉም የኦሮሞ ዜጋ ይህንን የጠላት ሴራ ለማምከን ከያለበት ሁሉ የጠላትን ጥቃት መመከት የዜግነት ግዴታ መሆኑን ተገንዝቦ መነሳት ኣለበት።

የኦሮሞ ህዝብ በሃገሩና በመሬቱ ላይ ባለቤት ሆኖ በሰላም መኖር የሚችለው በሃይል ለጭቆና ኣገዛዝ የዳረጉትን ኣሽቀንጥሮ ሲጥል ብቻ ነው። **"ለጭቆና ፍጻሜ ማበጀት ኣለብን!"** በሚል ካሁን ቀደም ባሳለፈው ቆራጥ ውሳኔ በመጽናት ኣመጹን ማፋፋም ብቻ ነው ዘላቂና ኣስተማማኝ መፍትሄ የሚያስገኝለት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከዚህ መንግስት ጋር በመሰለፍ የዚህን ጸረ-ህዝብ ስርዓት እድሜ ለማራዘም በመጣር ላይ የሚገኙ ዜጎች ወያኔ በህዝባቸው ላይ እየፈጸመ ያለውን ጠላታዊ ተግባር እያዩ ዝምታን መምረጥ በጠላት ዘንድም የሚያስንቃቸው መሆኑን መረዳት ይገባቸዋል። በወያኔ ጦር ሃይል ውስጥ በመሰለፍ ለጠላት ክንድ የሆኑ የኦሮሞ ዜጎች ኦሮሞን መሬትና ሃብት ኣልባ እያደረገ እንዲሁም ህይወቱን እየቀጠፈ ያለውን ጦርነት እያዩና እየሰሙ ኣስፈላጊውን እርምጃ ኣለመውሰድ ያስጠይቃቸዋል። ዛሬ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መዋቅርና ቄሮ ኦሮሞ፣ እናቶችና ኣባቶች ባዶ እጆቻቸውን ጠላትን እየተጋፈጡ ባለበት ወቅት ለጠላት መሳሪያ ኣንግቶ ዘብ መቆም ኣሳፋሪ ነው። በመሆኑም ለህዝባችን እንጂ ለባዕዳን ኣንሰለፍም በማለት እልቂት እየተፈጸመበት ካለው ህዝባቸው ጎን እንዲቆሙ ኦነግ ጥሪውን ያስተላልፍላቸዋል።

የወያኔ መንግስት እንደማናቸውም ኣምባገነን መንግስታት ጠንካራ መስሎ ለመታየት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት እድሜውን ለማራዘም ይጥራል። ይሁን እንጂ ይህ ፈጽሞ እውን ሊሆን ኣይችልም። የሚፎክርበትና ህዝቦችን የሚያስፈራራበት ሃይል ለጊዜው ሊያቆየው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ የወገናቸውን ጉዳትና ሰቆቃ እያዩ እስከመጨረሻ ከስርዓቱ ጋር ይሰለፋሉ ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል። ይህ በወገናቸው ላይ የሚፈጸመው ወሰን ያጣ በደልና ጭቆና ኣፈሙዛቸውን ወደ ጨቋኙ መንግስት እንዲያዞሩ ያስገድዳቸዋል። በተለይዩ የመንግስት መዋቅሮች ውስጥ በመታቀፍ ጸረ-ህዝብ የሆነውን መንግስት እያገለገሉ ያሉትም ካሁን በኋላ ይበቃል! ብለው ከህዝባቸው ጋር እንደሚሰለፉ ጥርጥር የለም።

በዚህ መንግስት ስር የህዝቦች መብቶች እንደማይከበሩ የታወቀ ነው። በመሆኑም ያለው ብቸኛው ኣማራጭ ይህንን መንግስት ማስወገድ ነው። **ለዚህም የኦሮሞ ህዝብ እያካሄደ ያለውን የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ መቀጠል ብቻ ነው የሚፈልገውንና የሚመኘውን መፍትሄ የሚያስገኝለት። በመሆኑም ዛሬም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የኦሮሞ ህዝብ ከሁሉም ኣቅጣጫ ኣመጹን በማፋፋም ለወያኔ መንግስት ፍጻሜ እንዲያበጅለት ጥሪውን ያድሳል።** የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ባያለበት ሁሉ የኦሮሞን ህዝብ ጠላት በማጥቃት ግዴታውን መወጣቱን እንዲቀጥል መልዕክቱን ያስተላልፋል። የኦሮሞ ወጣቶች፣ ቄሮ ኦሮሞም ስርዓቱን ለማቆየት እየተሯሯጠ ባለው የወያኔ/ሕወሃት መንግስት ላይ በመላው ኦሮሚያ ኣመጽ በማቀናጀት እድሜውን በማሳጠሩ ውስጥ ድርሻውን እንዲወጣ ኦነግ ያሳስባል።

በውጪ ሃገራት የሚኖረው የኦሮሞ ህዝብም ህዝባችን የሚገኝበትን ሁኔታ ክብደት በመገዘብ ጊዜና ሃብቱን የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም ሊያስከብር በሚችል ጉዳይ ላይ በማዋል የመፍትሄ ምንጭ እንዲሆን ኦነግ መልዕክቱን ያስተላልፋል።

የኦሮሚያ ኣጎራባች ተጨቋኝ ህዝቦችም ሆኑ ሌሎች ጠላት በሚሸርበው ሴራ ተታልለው እርስበርሳቸው ከመጋጨትና ከመናቆር በመቆጠብና ወያኔ ከሚያናፍሰው የውሸት ማስፈራሪያ ፍርሃትና ጥርጣሬ ነጻ ሆነው በጋራ ጠላታቸው ላይ ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ኦነግ በድጋሚ ያሳስባል።

ዘወትር ጭቆናን እያስተናገዱ መኖር እዚህ ላይ ማብቃት ኣለበት። ከሁሉም ቦታ በኣንድነት የተፋፋመው ኣመጽና የተካሄደው ትግል የኦሮሞ ህዝብ ሃይል መሆኑን ኣሳይቷል። በመሆኑም ኣሁንም በኣንድነት በመነሳት ጠላትን በማስወገድ ለጨቋኝ መንግስት ፍጻሜ እናብጅ። ለጊዜያዊ ጥቅም በሚል ለችግር ጊዜ በደረሰላቸው የኦሮሞ ህዝብ ላይ ክፋት እየፈጸሙ ያሉትንም ኣደብ እንዲይዙ በማድረግ መሬታችንና ማንነታችንን እናስከብራለን።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ጥር 21፡ 2017ዓም**